ኢስላም ረሒመሁሏሁ ተዓላ –የፍልሚያው ዕለት ሁለቱም ሠራዊቶች መፋለም ጀምረው ሳለ እንዲህ አሉኝ ፦ "እገሌ ሆይ! ምት ካለበት ገብቼ እንድፋለም የምት ምድብ ላይ መድበኝ "አሉኝ ።» ከጠላት ፊት እንዲፋለሙ ቦታ ሰጠኋቸው ። ጠላቶች በወቅቱ ሰይፎቻቸው ከአቧራው ግርዶሾች ውሰጥ አልፈው ሲያብረቀርቁ ይታዩ ነበር ። እንደነርፍም ግር ብለው በመትመም ወደኛ እያሰገመገሙ በመሮጥ ላይ ነበሩ ። ከዚያም እኔ « አለቃዬ! ይህ አሁን የመደብኮት ቦታ የምት ምድብ ነው ። ጠላትም ከዚህ አቧራ ውሰጥ እየተንደረደረ ወጥቶ ከዚህ ቦታ የቆመውን ሰው ከመግደል ውጭ ሌላ በምሕረት አያልፋትም ። ምትን ሊጋፈጡ ይሽው እንደተመኙት ከዚህ መድቤዎታለሁ » አልኳቸው ። ከዚያም ፍሊሚያው ተጧጧፈ ፣ አቧራውም ጨሰ ፣ ጦርነቱ ጋለ በእኔና በእርሳቸውም መካከል ፍልሚያው ለያይቶን እንዳንተያይ ጋረደኝ ። አሏህ ድል አቀዳጀን ። ከፍ ባለ ድምፅ ሠራዊቱን የሚያነቃቁ እና የሚያበረታቱ ፤ ከጦር ሜዳው መሸሽ የሚያስከተለውን ፍድዳ በማስጠንቀቅ ሠራዊቱን በፍልሚያው ላይ እንዲበረቱ የሚያጸኑ የሁለት ሰዎችን ድምፅ አሰማ ነበር ። አሻግሬ ሰመለከት ሸይኹ እና ወንድማቸው ነበሩ ። » ብሎ ተረከልኝ )) ይላሉ ። [57] እኒህ ታላቅ ሰብእና በዚህ ዓይነቱ ክስተት ላይ ያስመዘገቡት ገድል ሕይወታቸውን በብዕር እና በአንደበት በማስተማር ብቻ ያልገቱ የጦር ሜዳም ጀግና እንደነበሩ ታሪካቸው ያረጋግጥልናል ።

## በዕውቀት የነበራቸው ማዕረግ እና ዑለሞች ስለርሳቸው ሰብእና የሰጡት ማረጋገጫ

ሸይኹል ኢስላም ኢብኑ ተይሚየህ ረሒመሁሏሁ ተዓላ በዕውቀታቸው ሁሉን አቀፍ የዕውቀት ባለቤት በመሆን ታላቅ ሰብእና ለመሆን የበቁ ብርቅዬ ሰው ናቸው ። በዘመናቸው የነበሩትን ተፎካካሪዎቻቸውን በሙሉ በሁሉም መስክ አንበርክከው የአዋቂዎች አዋቂ የሊቃውንት ሁሉ መሪ የሆኑ ሊቅ እንደሆኑ ማስመስከር ችለዋል ። በእርግጥ ሰብእናቸው የተሟሏ ኢማም ፣ ሁለመናቸውን ለእስልምና የቸሩ ሸይኹል ኢስላም ፣ ኢስላማዊ መርሆችና የእምነት አመለካከት በአደገኛ ማዕበል ከመናወጥ

ደርሰው የታደጉት የኢስላም አለኝታ ፣ ምንም የማይወዘውዛቸው ጽኑ የኢስላም መከታ ናቸው ። ኢማም ቢሉ ተራ ኢማም አይደሉም ። የእርሳቸው መጽሐፍት ጨለማ ከደረሰበት ሥፍራ ሁሉ ደርሶ የድንቁርናን ጽልመት በመግፈፍ ሌሊቱን በዕውቀት ብርሃን ብሩህ ቀን አድርገውታል ። ጎጠኝነትን ርቀው የሰለፎችን ጎዳና ብቻ ይዘው ሚዛናዊ ዕርምጃን ተራምደዋል ። ከወገንተኝነት የጸዳን የእምነት መንገድና የዲን መመሪያ ይዞ የሚራመድ ሁሉ የኢብኑ ተይሚየህን መዝሃብ ነው የተከተለው እየተባለ ይነገርላቸዋል ። በዚህም ገድል የትውልዶች ትምህርት መቅሰሚያ ማዕከል እንጂ አንድ ተራ ዓሊም ወይም ግለሰብ ብቻ አይደሉም ። ከእርሳቸው ፍትሐዊ የትምህርት ማዕከል ፤ በሚዛናዊውም ተቋም በርካታ ሊቃውንት ዕውቀትን ገብይተው ተመርቀውበታል ። አያሌ ኢማሞች ተኮትኩተው አድገው ለፍሬ በቅተዋል ።

የሸይኹል ኢስላም ኢብኑ ተይሚየህ ረሒመሁሏሁ ተዓላ ዘመን በተለያዩ አመለካከቶች በተገመዱ የአመለካከት ወጀቦች እስልምና ዙሪያውን የተከበበት ወቅት ነበር ። እያንዳንዱ ወጀብ ከእስልምና የእምነት ጸዳል ያፈነገጡና ከባዕድ የእምነት አካላት አቋም የተበካከሉ አመለካቶችን ጠራርጎ በማምጣት ነበር የኢስላምን ጸዳል ከፉኛ የመቷት ። በወቅቱ ጀህሚየህ ፣ አሻዒራ ፣ ሙዕተዚላ እና ሌሎችም አንጃዎች በእስልምና ዙሪያ ተኮልኩለው ቀስ በቀስ ከየአግጣጫው ሸርሸረው ሊንዱት የሰፈሩበት ወቅት ነበር ።በወቅቱ ሱፊዮች በነቀዘው የአመለካከት እና የእምነት አቋሞች እስልምና ምህዋር ውስጥ ዘልቀው በመግባት ድንኳኖቻቸውን መደኮን የቻሉበት ብርቱ ሞገደኛ ወቅት ነበር ። የግሪክና የፋርሳውያን የፍልስፍና አቋም አራማጆች የሱፊዮችን ድንኳን መጠለያ አድርገው የኢስላምን መርሆዎች ሸርሸረው የራሳቸውን ርእዮት የሰገሰጉበት አደገኛ ወቅትም ነበር ። አመለካከትንና የእምነት መርሆችን የማንቀዝ ሥርዓት ለማስፈን ሁለ-ገብ ዘመቻ በመስቀላውያን ጦረኞች መታጀቡ ደግሞ ሙስሊሞች በወቅቱ የነበሩበት ሰቆቃ ከድካው መድረሱን ያስረዳል ። ሸይኹል ኢስላም ኢብኑ ተይሚየህ ረሒመሁሏሁ ተዓላ እነዚህን ሁሉ በሙሉ ቆራጥነትና በማይናወጥ የኢማን ጽናት ተጋፍጠው እስምናን እና ሙስሊሞችን ታድገዋል ። እያንዳንዱ ሞገደኛ ይዞት

የመጣውን ጸረ- ኢስላም አመለካከት ወደመጡበት በመመለስ አቀንቃኞቻቸው አንገታቸውን ደፍተው የሐፍረትን ማቅ ተከናንበው እንዲያቀረቅሩ አድረገዋቸዋል ።

ስለ አንድ የሙያ ዘርፍ አንስተው ሲናገሩ ለሰማቸው ሰው በዚያ የሙያ ዘርፍ ብቻ ልዩ የሆነ የእውቀት ምጥቀትን ተችረዋል ብሎ ነበር የሚገምታቸው ። በሁሉም የሙያ ዘርፍ - ሸሪዓዊውም ይሁን ከሸሪዓ ውጭ ያሉ አጠቃላይ ዕውቀቶችን በተመለከተ- የነበራቸው ዕውቀት ምሉዕ እና ከላዕላይ የዕውቀት ጉልላት ላይ የደረሰ በመሆኑ ሁሉም ባለሙያ በዕወቀታቸው ተደምሞ እና በትንግርት ነበር የሚያቸው ። [58]

ስለሸይኹል ኢስላም ኢብኑ ተይሚየህ ረሒመሁሏሁ ተዓላ ማንነት መናገር የሚችሉት በዕውቀት ምጥቀት ውስጥ የላዕላይ ደረጃው ላይ የደረሱት ብቻ እንጂ ሌሎች አይደሉም ። ሊቃውንት -በእርግጥም የሊቅነት ደረጃ ምን እንደሆነ የገባቸው ሊቃውንት ብቻ - ስለ ሸይኹል ኢስላም ኢብኑ ተይሚየህ ረሒመሁሏሁ ተዓላ ልዩ ስብእና መግለጽ ይችላሉ ። እነሆ ከውዳሴች ባህር ጥቂቱን እንመልከት :

ቀንደኛ ጠላታቸው የነበሩት ሸይኽ ከማሉዲን ዘምለካኒ የተቀኙትን ማረጋገጫ እነሆ በቀላል አማርኛ ተርጉሜዋለሁ !!

*ቃላት ሊይገኝም እርሱን ምገልጽበት*
*ይታሰራል በእርሱ ከመግለጽ ለንደበት*
*ባህሪው ድንቅ ነው ቆጥረው የማይዘልቁት*
*የአሏህ ሑጅጃ ነው ታግለው ማይበግሩት*
*እርሱ ወደር የለው ሆኖብናል ትንግርት*
*ብርሃን ፈንጥቆ ሲወጣ በንጋት*
*ጨለማውን ገፍፎ ብርሃን እንደሞላት*
*ምድርን በዕውቀቱ እንዲህ ሊደመቃት*
*ባለታላቅ ማዕረግ የሊማሞች አባት*
*ኢብኑ ተይሚያህ ነው ወደር የታጠለት !!*

በተጨማሪም «ረፉዑል መላም ዓን አኢመቲል አዕላምኝ» በተሰኘው መጽሐፍ ውስጥም እኒሁ ሸይኽ - ማለትም ሸይኽ ከማሉዲን ዘምለካኒ - መጽሐፉን ስለጻፉት ሸይኹል ኢስላም በራሳቸው እጅ ጽሑፍ በጻፉት ማስታወሻ ሲገልጹ፡– (( ይህ መጽሐፍ ፡ የሸይኽ አል–ኢማሙል ዓሊም ፣ በዕውቀቱ ወደር ያልተገኘለት ሊቅ ፣ ሸሪዓዊ ቅርሶችንና ትውፊቶችን በመንከባከብ ጠብቆ በማኖሩ ዓለም የሚመሰክርለት ትጉህ የኢስላም አለኝታ ፣ ዛሂድና ዓቢድ = ከዱንያ ጥቅማጥቅሞች አራሱን የቆጠበ አና አሏህን በመግገዛት ላይ የተመጠደ ዓይነተኛ የአሏህ ሎሌ ፣ ለሁሉም ሊቃውንት ተምሳሌት የሆነ ፣ የኢማሞች ኢማም ፣ ሙስሊሞች በሙሉ ፈለጉን የሚከተሉት ሁነኛ ተምሳሌት ፣ ከውለሞች ሁሉ የበላይ ዓሊም ፣ የነብያት ወራሽ ፣ ድካ የደረሰ ሙጅተሂድ ፣ በጣት ከሚቆጠሩ የላቁ የኢስላም ልጆች ውስጥ አንደኛው ፣ የአስልምና በረከት ፣ የዕውቀት ዋቢ ፣ የተናጋሪዎች ፈርጥ ፣ የሙብተዲዖች ጠንቅ ፣ ሱንናን ሕያው ያደረገ ጅግና ፣ አርሱን አሏህ ለኛ በመቸሩ ውለታው የከበደብን ባለዕዳዎችም ያደረገን ድንቅ የአሏህ ሰጦታ ነው ። በአርሱ አስተምሮ ምክኒያት በጠላቶቹ ላይ ማሰረጃ ተቆጥሯል ፣ በአርሱ በረከት አና ቅን የሆነ ዕርምጃ የሐቅ ማሰረጃ በሙሉ ይፋ ሆኖ አንዲወጣ ያደረገው ተቂዩዲን አቢል ዓባስ አሕመድ ብኒ ዐብዲልሐሊም ብኒ ዐብዲሰላም ብኒ ተይሚየተል ሐራኒይ የጻፈው መጽሐፍ ነው ። አሏህ ደረጃውን ያልቀው ፣ በአርሱም የዚህን ዲን ዋልታዎች አሏህ ያጠንክራቸው )) በማለት መጻፋቸውን አንብቤያለሁ ይላሉ ኢብኑ ዐብዲልሃዲ ። [59]

አልኢማም አዝዘሃቢ ሸይኹል ኢስላም ኢብኑ ተይሚየህ ረሒመሁሏሁ ተዓላ ማን እንደሆኑ ሲገልጿቸው (( ... ሸይኹል ኢስላም ኢብኑ ተይሚየህ ረሒመሁሏሁ ተዓላ የአርሳቸው ሸይኾች በሕይወት አያሉ ከታላላቅ ሊቆች ተርታ መሰለፍ ችለዋል ። በቅፍለት የሚጫኑ መጽሐፍትን መጻፍ ችለዋል ። ለመጽሐፍነት የተዘጋጁ ማስተወሻዎቻቸው አራት ሺህ ኩራሶች[60] አና ከዚያ በላይ ይሆናሉ ። ለበርካታ ዓመታት ቁርአንን በየጁምዓው በማብራራት ያስተምሩ ነበር ። ተፍሲር ሲፈስሩ የመጠቀ ዕውቀታቸው ጎልቶ ይስተዋላል ። ከበርካታ መሻይኾች አንደበት ሐዲስን

በመሰማት በልባቸው አትመው አኑረዋል ። የሐዲስ መሻይኾቻቸው ከሁለት መቶ በላይ ናቸው ። የተፍሲር ዕውቀት በእርሳቸው በቃ ። የሐዲስ ሰዎችን በማወቅ ተፎካካሪ የታጣላቸው የሙሐዲሶች ፈርጥ ናቸው ። ደካማ ሐዲስን ከትክለኛው ሐዲስ በማበጠርና ተያያዥ ጉዳዮችን በይነው በመግለጽ ወደር የላቸውም ። የአራቱን ኢማሞች መዝሃብ ከነጥቅንቅን ጉዳዮቻቸው ለይቶ ማወቁ ይቅርና የሰሃቦችና የታቢዒኖች መዝሃብን እንኳን ከነጥቅንቅን ነጥቦቻቸው አንጥሮ በማወቁ ሊቃ ኢይገኝላቸውም ። የተለያዩ ባዕድ አመለካከት ያላቸውን ጭፍሮች የአመለካከት መርሆዎችና መሠረታዊ ሕግጋቶቻቸውን ጠንቅቀው በማወቁ ረገድ ፣ ኡሱሎችን ፣ የሥኑ-አመከኒዮ ዕውቀትን በተመለከተ ያላቸውን ዕውቀት የእርሳቸውን ምጠቅት ሊደርሰበት የሚችል ሰው በፍጹም አላውቅም ። ...)) ብለውላቸዋል ።

በተጨማሪም (( በአእምሮ ብሩህነትና በመግንዘብ ፍጥነት የአሏህ ተአምር የሆኑ የፍጥረታት ትንግርት ናቸው ። ቁርአንን ፣ ሱንናንና የኢ ኽቲላፍን ዕውቀት በማወቅ የአዋቂዎች ሁሉ ቁንጮ ናቸው ። ማስረጃዎችን ከነዘጋቢዎቻቸው ከአእምሯቸው ማህደር በማውጣት እንደወረደ በማስቀመጥ ማንም አይስተካከላቸውም ። በዘመኑ ተቀናቃኝ ያልተገኘላቸውት ብቸኛው ወደር የለሽ ሊቅ እና ዛሂድ ሸይኹል ኢስላም ኢብኑ ተይሚየህ ረሒመሁሏሁ ተዓላ ናቸው ። )) (( በሚደንቅ ፍጥነት ፣ ቅልጥፍናና ምጥቅት ነበር የተማሩት ። በፊቅህና በሐዲስ ጥልቅ ዕውቀት ድካ ደረሰዋል ። ዕድሜያቸው አሰራ ሰባት ሳይደርስ ለማስተማር እና ለፈትዋ ብቁ የሆኑ ከአላህ ፍጥረታት ውስጥ የፍጥረታት ትንግርት ናቸው ። የተፍሲርና የኡሱል ትምህርቶችንና የሌሎችንም የዕውቀት ዘርፎች በሙሉ ጠንቅቀው በማወቅ የቀዳሚነትን ማዕረግ በማግኘት ሊቃውንትን መምራት ችለዋል ። ... ተፍሲር ከተነሳ ሰንደቁ በእጃቸው ነው ። ፉቀሃዎች ሲወሱ እርሳቸው ከፊቅህ ጉልላት ላይ በመዋል ወሰን የለሽ ሙጅተሂድ መሆናቸውንና ከሰገነቱ ላይ ከፍ ብለው መደላደላቸውን ሁሉም ያስተውላል ። ሑፋዞች ተጥደው በቃል የያዙትን ኢስላማዊ ቅርስና ትውፊት እንዲናገሩ ዕድል ተሰጥቷቸው መናገር ጀምረው ያላቸውን እንዳሟጠጡ እርሳቸው ከመጅሊሱ ሲመጡ

ሑፋዞች አፋቸው ተለጉም የሚናገሩትን በማጣት አርሳቸው ብቻ እንዲናገሩ መድረኩን በአከብሮት ይለቁና በዐጀብ አፋቸውን ከፍተው ሸይኹል ኢስላም ኢብኑ ተይሚየህን ረሒመሁሏሁ ተዓላ በማድመጥ በሒፍዛቸው ይመሰጣሉ። አርሳቸው በትነው ሲናገሩ አነርሱ አጥፍጥፍ ብለው ይቀመጣሉ ፤ አርሳቸው የተብቃቃ ትውፊትን ሲያቀርቡ አነርሱ ከአርሳቸው ከጃዮች በመሆን እንደአዲስ ትውፊትን በመሐፈዝ ይወስዳሉ ። ሥነ-አመክንዮ ዐዋቂዎች በሥነ-አመክኒዮዋቸው ዕውቱ አርሳቸው እያሉ አውቀናል በማለት አይኩራሩም ምክኒያቱም አርሳቸው በሥነ-አመክንዮ ዕውቀት የሚፎካከር አቻ የላቸውም ፣ አነርሱ ዋቢ መሆን ሲጠበቅባቸው በአንጻሩ ግን አርሳቸው ነበሩ ዋቢያቸው ። ኢብኑ ሲና ፈላስፋዎችን በዕውቱ አርከን ጥሎ ከማማው ላይ ወጥቷል እያሉ ቢፎክሩ አርሳቸው ፍልስፍናን እንደሚያውቅ መናገር ሲጀምሩና የፈላስፎችን ገመና በመግፈፍ አርቃን ሲያስቀሯቸው ምስክር ይሆናል ። ዐረቢያን በማወቅ ፣ በግስ አርባታ ዕውቱትና በሰዋሰው ዕውቱ አቻ የላቸውም ። አርሳቸው እኔ ከምገጸቸው በላይ የላቁ የምሉዕነትን ሰብእና የተላበሱ ድንቅ ሰው ናቸው። ብዕሬ ስለርሳቸው ለመግለጽ ትብረከረካለች ፤ ለመጻፍም ትወለጋገዳለች ። ... ))

(( የቁርአን ፣ የሱንና እና የሙስነድ ዕውቀቶች በሙሉ ዋቢ ናቸው ። ዕውቱን የማካበቡ ብቸኛ ሥልጣን የአሏህ ብቻ ነው ። ይሁንና የሐዲስን ዕውቀት በሙሉ አካብበዋል ባንልም «ኢብኑ ተይሚየህ የማያውቀው ሐዲስ ሐዲስ አይደለም » የሚለው ገለጻ የአርሳቸውን የመጠቀ የሐዲስ ዕውቀት ገለጭ ነው ። አርሳቸው ዕውቀትን ከባህሩ ጠግበው የጠጡት ሲሆን ሌሎች ከባህሩ ገባሮች ነው የተጎነጩት ። (( በሩከንና በመቃም መካከል ቆሜ «በዓይኖቼ አርሳቸውን የሚመስል የዕውቀት - ዳር አላየሁም » ብዬ ብምል መሃላዬ ኩነኔ አይሆንብኝም ። አርሳቸውም እንኳን አራሳቸውን የሚመስል ሊቅ በሕይወት ሳሉ በዓይናቸው አልተመለከቱም ። )) በማለት ነው ምስክርነታቸውን የገለጹት ። [61]

ሸይኽ ተቂዩዲን ኢብኑ ደቂቅ አልዒድ ስለ ሸይኹል ኢስላም ኢብኑ ተይሚየህ ረሒመሁሏሁ ተዓላ ተጠይቀው የሰጡት ምላሽ፡– (( *የዕውቱት ዘርፎች በሙሉ በዓይኑ ውስጥ የሚዘዋወሩ ግለሠብ ፣ ከዓይኑ ሰሌዳ አሰፍሮ ያኖራቸውን የማይነጥፉ የዕውቱት ትውፊቶች ከፈለገው የዕውቱት ዘርፍና ዓይነት የሻውን ወስዶ በረቀቀ አንደበት የሚያስራዳ የሻውን በመተው የሻውን በትኖ የሚዘረዝር የዕውቱትን ባሕር ... በዓይኔ ተመለከትሁ* )) የሚል ነበር ።[62]

ሸይኽ ኢብኑ ዐብዲልሃዲ፡– (( *አንድ ግለሠብ (ሸይኹል ኢስላም ተቂዩዲን ኢብኑ ተይሚየህ ረሒመሁሏሁ ተዓላ ) በአንድ ቀን ውስጥ አንድ ጥራዝ መጽሐፍ እንዳጻፉ ፣ በሌላም ቀን በአንድ መጅሊስ አርባና ከዚያ በላይ የሚሆን ወረቀት ያለው ጥናት እንደጻፉ ፣በጣም ውስብስብ ለሆነ ርዕሰ ጉዳይ በአንድ ቀን ውስጥ የጻፉትንና ጠርዘው ያስቀመጡትን ሰቆጥር ሰምንት ኩራስ ሆኖ አግኝቸዋለሁ ። ለአንድ ጥያቄ መልስ አንድ ጥራዝ መጽሐፍ የሚጽፉበትም ቀን አልለ ።* )) [53]ብሎ ነግሮኛል። በማለት መጽሐፉቸው ውስጥ ዘግበዋል ።

እነዚህ ከላይ የጠቀስናቸው ባህር ከሆነው የውዳሴ መዝገብ በትንሽ ማንኪያ ጨለፍ አድርገን ያስነበብናችሁ የውለሞች ውዳሴ ነው ። በነዚህ የውለሞች ውዳሴ ሸይኹል ኢስላም ተቂዩዲን ኢብኑ ተይሚየህ ረሒመሁሏሁ ተዓላ የተቸሩትን ወሰን የለሽ ዕውቀት እና ማዕረግ መግገንዘብ ይቻላል ። ስለርሳቸው ስብእና በውለሞች ዘንድ የነበራቸውን ታላቅ ማዕረግ ፣ ክብርና ቦታ በ817 ገጽ የታጸፈው ታሪካቸውን በሙሉ አጠናቅሮ በያዘው መጽሐፍ ውስጥ ያገኙታል ። መጽሐፉም «*ኣልጃሚው ሊሲረቲ ሸይኺል ኢስላም ኺላለ ሰብዓቲ ቁሩኒ*» ይሰኛል ።

እኒህ ታላቅ ሰው ከእስልምና በተለያዩ ሰርጎ ገብ አመለካከቶችና ባዕድ ዕርምጃዎች የተሸረሸረውን ኢስላማዊ ሥርዓት መልሰው በመገንባትና ወደቀድሞ ይዘቱ መመለሳቸው ብቻ የታላቅ ክብር ባለቤት እና ከፍ ያለ የልቅና ማዕረግ ያላቸው የተሃድሶ አርበኛ እንዲሆኑ ያስችላቸዋል ።